810 ሀሀ250/54

22/06/2009

745/2013

ለከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ
ከ/ል/ቤ/ሚ/ር

ጉዳዩ፡ **የጸደቀ መመሪያ ስለመላክ**

7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የኢግዚቢሽንና የከተሞች ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 57/2009 ሆኖ ከየካቲት ወር 2009 ዓ.ም ጀምሮ በሚኒ ካቢኔ የጸደቀ መሆኑ ይታወቃል፡፡

`በዚሁ መሠረት የመመሪያውን ተፈጻሚነት እንድትከታተሉና እንድታስፈጽሙ የጸደቀ 1 ጥራዝ መመሪያ (ሰነድ) ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ የተላከ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

አምባቸው መኮንን ሲሳይ (ዶ/ር)
ሚኒስትር

ግልባጭ
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ (የከተማ ልማት ዘርፍ)
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ (የመኖሪያቤቶች ልማትና አስተዳደር ዘርፍ)
- ለሚኒስትር ጽ/ቤትና ሚኒ ካቢኔ ጉዳዮች ቢሮ
- ለሕግ ዳይሬክቶሬት
  ከ/ል/ቤ/ሚ/ር

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND HOUSING

# የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር

# 7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የኤግዚቢሽንና የከተሞች ምዝገባ

# መመሪያ ቁጥር 745/2013

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም

Ethiopian Urban Forum

የካቲት 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣

## መግቢያ

በኢትዮጵያ ፈጣን የከተሞች መስፋፋትን ተከትሎ የከተማ ነዋሪዎችንና የሌሎች ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በማጠናከር መልካም ተሞክሮዎችንና ልምዶችን በማስፋፋት የከተማ ልማት ፖሊሲውን እና የከተማ ልማት ፕሮግራሞችን ትግበራና ስኬት ማፋጠን ይቻል ዘንድ የከተሞች ቀን፣ ሳምንትና ፎረም በመባል ተሰይሞ በተለያዩ ከተሞች አስተናጋጅነት በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲከበር የቆየ ሲሆን በ2009 በጀት ዓመት በዓሉን በጎንደር ከተማ ለማክበር ከፍተኛ ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል፡፡

7ኛው የኢትዮጵያ የከተሞች ፎረም ኤግዚቢሽን በተደራጀና ወጥ በሆነ ሁኔታ ከዝግጅት እስከ ፍፃሜ እንዲቀጥል ለማድረግ እስከ 6ኛው የከተሞች ፎረም ድረስ የተገኙ ተሞክሮዎች እና በዩ ኤን ሃቢታት አማካኝነት የአለም የከተሞች ፎረም የኤግዚቢሽን ዝግጅት ልምዶችን በማካተት አጠቃላይ አቅጣጫ እና የትኩረት መስኮች በሚያመላክት መልኩ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

በኤግዚቢሽን ዝግጅቱ ከተሞች በዋና ዋና የከተማ አጀንዳዎች ዙሪያ በእድገት ጎዳና ለለውጥ እያደረጉት ስላለው ጥረት፣ ስላስመዘገቧቸው ስኬቶች፣ ስለገጠሟቸው ተግዳሮቶች እና ሌሎችም ተያያዥ ጉዳዮች በተሞክሮነት ሊወሰዱ የሚችሉ ስራዎቻቸውን ማራኪና በቀላሉ መልዕክት ማስተላለፍ በሚችል አቀራረብ ለህዝብ ክፍት በማድረግ መደበኛ ያልሆነ የእርስ በርስ ውይይቶች መነሻ ነጥብ እንዲሆን በማስቻል የእውቀት ልውውጥ የሚፈጠርበት ነዉ፡፡

ይህን ለማድረግም የኤግዚቢሽን ዝግጅቱና አቀራረቡ ከዚህ በፊት ይካሄድበት ከነበረበት አካሄድ ለውጥ በማድረግ በተረጋጋ ሁኔታ መረጃ በሚሰጥና መልእክት በሚያስተላልፉ የተለያዩ ፎቶግራፎች፣ ስታንዶች፣ ዶክመንተሪዎች እና መሰል የማቅረቢያ ዘዴዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራበት ይሆናል፡፡

ይህ መመሪያ የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ኤግዚቢሽንን በሚመለከት ለተሳታፊ ከተሞች ጠቃሚ መረጃ በመስጠት፤ የአዘጋጆችን፣ የተባባሪዎችን እንዲሁም የተሳታፊዎችን ሚና በመለየት በጎንደር ከተማ ለሰባተኛ ጊዜ የሚከበረውን የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የኤግዚቢሽን ሥራው የሚመራበትን ስርዓት ለመደንገግ የተዘጋጀ ነዉ፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር "የ7ኛው የኢትዮጵያ የከተሞች ፎረም የኢግዚቢሽን ዝግጅትና የከተሞች ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 745/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ:-

1) "ከተማ" ማለት ማዘጋጃ ቤት የተቋቋመበት ወይም ሁለት ሺ. እና ከዚያ በላይ የህዝብ ቁጥር ያለው ሆኖ በሰባተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ላይ የሚሳተፍ ከተማ ወይም ተቋም ነው፡፡

2) "አዘጋጅ ከተማ" ማለት የሰባተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የሚካሄድበት የጎንደር ከተማ ነው፡፡
3) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሰባተኛዉ የከተሞች ፎረም አዘጋጆች፣ ተባባሪ አዘጋጆችና ተሳታፊ ከተሞች እንዲሁም በዝግጅቱ በሚሳተፉ ሌሎች የመንግስትና የግል ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 4. ዓላማዎች

1) ከተሞች የልማት ስራዎቻቸውን የሚያሳዩበትና ገጽታቸዉን የሚገነቡበት፣ እርስ በእርስ የሚማማሩበት፣ ለኗሪዎቻቸው እና ለሌሎች ባለ ድርሻ አካላት አስፈላጊ መረጃ የሚሰጡበት መድረክ ለማመቻቸት፤
2) ከተሞች የኢንቨስትመንት፣ የኢንዱስትሪ፣ የቱሪዝም፣ የገበያ እና ሌሎች መስህቦቻቸውን የሚያስተዋውቁበት መድረክ በመፍጠር ለዕድገታቸው መፋጠን አጋዥ የሚሆኑ ግብዓቶችን እንዲያገኙ ለማስቻል፣ እና
3) ከተሞች ራሳቸውን በብቃት በማስተዋወቅ የእርስ በርስ ጤናማ የውድድር መንፈስ ለማዳበር ነው፡፡

## 5. ከኤግዚቢሽኑ የሚጠበቁ ውጤቶች

1) ስለ ከተሞች የልማት ሂደት እና ስለደረሱበት የዕድገት ደረጃ በነዋሪዎች እና በሌሎች ባለድርሻ አካላት ትክክለኛ ግንዛቤ ይፈጠራል፤
2) ከተሞች የልማት መስህቦቻቸውን በማስተዋወቅ ከኢንቨስትመንት፣ ከቱሪዝም፣ ከገበያ ...ወዘተ ተጠቃሚነታቸው ይጨምራል፤
3) ከተማን የማስተዋወቅ ሂደት እና ጥቅሞቹን በሚመለከት ግንዛቤ ይፈጠራል፣ ብሎም ከተሞች እራሳቸውን የማስተዋወቅ ስራ እንደ አንድ ዓብይ ተግባር ቆጥረው ልምድ እንዲወስዱ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፣
4) የመረጃ ልውውጥን በማጠናከር በከተሞች እና በኗሪዎቻቸው መሀከል ያለው መግባባት እና ትስስርና የከተማ ህዝብ ተሳትፎ ይጠናከራል፤ ንቅናቄም ይፈጠራል፣

## 6. ኤግዚቢሽኑ የሚካሄድበት ጊዜ እና ቦታ

7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ኤግዚቢሽን ከሚያዚያ 22 - 28 ቀን 2009 ዓ.ም በጎንደር ከተማ ይካሄዳል፡፡

## ክፍል - ሁለት

## የተሳታፊ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### 7. የኤግዚቢሽኑ ተሳታፊዎች

1) ከተሞች የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ኤግዚቢሽን ከያዘው ከተሞችን የማስተዋወቅ ስራ ስራ እና በባለድርሻ አካላት ዘንድ ግንዛቤን የማስጨበጥ ዓላማ አካያ ለሁሉም የኢትዮጵያ ከተሞች ክፍት ይሆናል፡፡
2) በ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ኤግዚቢሽን ከሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የተውጣጡ ከ200 በላይ ከተሞች ይሳተፋሉ፡፡
3) ከሚመለከታቸዉ ከተሞች በተጨማሪ ለከተማ ልማትና ቤቶች ዘርፍ አጋዥ የሆኑ የሚከተሉት ባለድርሻ አካላት በኤግዚቢሽኑ መሳተፍ ይችላሉ፡፡

   ሀ/ የክልል ከተማ ልማትና ቤቶች ዘርፍ ተቋማት፣

   ለ/ አግባብነት ያላቸው የፌደራል ተቋማት፣

   ሐ/ አግባብነት ያላቸው የክልል ተቋማት፣

   መ/ የጥቃቅን እና አነስተኛ ተቋማት፣

   ሠ/ የቴክኒክና ሙያ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣

   ረ/ የፋይናንስ ተቋማት፣

   ሰ/ አግባብነት ያላቸው የግልና የመንግስት ተቋማት፣

   ሸ/ በከተማ ጉዳዮች ዙሪያ የሚሰሩ የሲቪል ማህበራት፣

   ቀ/ አለም አቀፍ እህት ከተሞች፣

   በ/ አለም አቀፍ ድርጅቶች፣

   ተ/ በኤች. አይ. ቪ/ ኤድስ፣ በስነ ተዋልዶና ማህራዊ ጉዳይ የተሰማሩ ድርጅቶች ናቸው፡፡

### 8. ዋና አዘጋጆች

የ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ኤግዚቢሽን ዋና አዘጋጆች የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር እና የጎንደር ከተማ አስተዳደር ናቸው፡፡

### 9. ተባባሪ አዘጋጆች

1) የ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ኤግዚቢሽን ጥራቱን በጠበቀና የከተሞችን ፎረም ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ማከናወን ይቻል ዘንድ በኤግዚቢሽን ዝግጅት በቂ ችሎታና ልምድ ያላቸው ድርጅቶች ሁሉ በጨረታ እንዲወዳደሩ በግልፅ ማስታወቂያ ይጋበዛሉ፤
2) የኤግዚቢሽን ተባባሪ አዘጋጅ የሚመረጠው ግልጽ በሆነ የውድድር መስፈርት እና ሂደት ብቻ ይሆናል፣
3) በጨረታ አሸናፊ ሆኖ የተመረጠው ድርጅት የሚጠበቅበትን ተግባር በበቂ ሁኔታ መፈጸም ይኖርበታል፤ በሚወጣው መርሀ-ግብር መሰረት ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር ውል ይፈራረማል፡፡

## 10. የፎረሙ ኤግዚቢሽንና የከተሞች ምዝገባ አስተባባሪ ንዑስ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1) የኤግዚቢሽኑን መሪ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣
2) ስለኤግዚቢሽኑ ኦፊሺያል መግለጫ ከመዝናኛ ዝግጅቶችና የኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች አስተባባሪ ንዑስ ኮሚቴ ጋር በመሆን አዘጋጅቶ መግለጫ ይሰጣል፣
3) የኤግዚቢሽኑን ተባባሪ አዘጋጅ የስራ ዝርዝር ቢጋር ያዘጋጃል፣
4) የኢግዚቢሽን ተባባሪ አዘጋጅ ቅጥር እንዲከናወን ያደርጋል፣
5) ለተሳታፊዎች ስለኤግዚቢሽኑ መረጃ ይሰጣል፣
6) ለኤግዚቢሽን ተሳታፊዎች የሚከራይ ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ ዋጋ ያለው የቦታ የዋጋ መጠን ያዘጋጃል፤ በከፈሉት የዋጋ መጠን የከተሞችን ምድብ ይወስናል፤ ቦታ በእጣ ይደለድላል፤
7) ኤግዚቢሽኑ የሚያርፍበትን ቦታ አርክቴክቸራልና ኤሌክትሪካል ፕላን በማሰራት እንዲጸድቅ ያደርጋል፣
8) የኤግዚቢሽን ተሳታፊዎች የሚፈልጉትን የቦታ መጠን እና የከተሞችን ጥያቄ መሰረት በማድረግ እና ክፍያ መክፈላቸውን በማረጋገጥ የቦታ ድልድል ይወስናል፣
9) ዘግይተው የሚመጡ ከተሞችን በመጠባበቅያነት ከተያዙት እና ለከተሞች ፎረም በዓል ዝግጅት ተመዝግበው ያልመጡ ከተሞች ድንኳኖች ክፍት መሆናቸውንና አገልግሎት አለመስጠታቸውን አረጋግጦ እንደ አመጣጥ ቅደም ተከተላቸው መስጠት እንዲቻል ለቴክኒክ ኮሚቴው የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፣
10) የኤግዚቢሽን ተባባሪው በሥራ ዝርዝሩ መሠረት ተግባሩን ማከናወኑን ይከታተላል፤ የኤግዚቢሽኑን አፈጻጸምም ይከታተላል።

## 11. የ7ኛው የከተሞች ፎረም አስተናጋጇ የጎንደር ከተማ አስተዳደር ተግባርና ኃላፊነት

1) ለኤግዚብሽን ዝግጅት ከ10 ሄክታር ያላነሰ በቂና አመቺ ቦታ አዘጋጅቶ ያቀርባል፤
2) ለኤግዚቢሽን ቦታ አስፈላጊ የሆኑ እንደ በቂ የኤሌክትሪክ ሀይል (3 phase)፣ የውሃ፣ የመኪና ማቆሚያ፣ የመጸዳጃ ቤቶች፣ አጥር ...ወዘተ የመሳሰሉ አገልግሎቶችን ያቀርባል፣
3) የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ፣ አምቡላንስ እና የእሳት አደጋ መከላከያ ያቀርባል፤
4) የተጠናከረ የጥበቃ ሥራ በማከናወን የኤግዘቢሽኑን ተሳታፊዎች እና የንብረቶቻቸውን ደህንነት ያስከብራል፣
5) ኤግዚቢሽኑን በከተማው ህዝብ በስፋት እንዲጎበኝ ለከተማው ነዋሪ፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች አደረጃጀቶች፣ ለአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መምህራንና ተማሪዎች፣ እንዲሁም የዩንቨርሲቲ ማህበረሰብ ወዘተ... የቅስቀሳ ስራ ያከናውናል፣

## 12. የ7ኛው የከተሞች ፎረም ኤግዚቢሽን ተባባሪ አዘጋጅ ተግባርና ኃላፊነት

በጨረታ የሸነፈዉ ተባባሪ አዘጋጅ ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱ በገባዉ ዉል የሚገለጽ ሲሆን የሚከተሉትን ዋና ዋና ጉዳዮች በትኩረት የሚያከናዉን ይሆናል።

1) ለኤግዚቢሽኑ ዝግጅት አስፈላጊ የሆኑ እንደ ድንኳን፣ የድንኳን ውስጥ የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ፣ ጠረጴዛና ወንበር ወዘተ የመሳሰሉ ቁሳቁሶችንና ሌሎች የኤግዚቢሽን አጋዥ መሳሪያዎችን ያቀርባል፤
2) የተሳታፊዎችን ጥያቄ ባገናዘበ መልኩ አርክቴክቸራል ፕላን ያዘጋጃል። ይህንኑም ለንዑስ ኮሚቴው አቅርቦ ያፀድቃል፤
3) በአርክቴክቸራል ወይም በስትራክቸራልና በኤሌክትሪካል ፕላኑ መሰረት ለሁሉም ተሳታፊ ከተሞች የድንኳን ተከላና ኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ያከናውናል፤
4) ኤግዚቢሽኑ የሚካሄድበትን ቦታ የማስዋብ ስራ (በዋና ዋና በሮች ላይ ሪቫን እና ሌሎች የማስዋቢያ ቁሳቁሶችን በመጠቀም) ይሰራል፣
5) ለከተሞች ኤግዚቢሽን ዝግጅት ሙያዊ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤
6) ተሳታፊዎች ከኤግዚቢሽን መክፈቻ ቀን በፊት ዝግጅታቸውን እንዲያጠናቅቁ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤
7) ከኤግዚቢሽኑ በፊት እና በኤግዚቢሽኑ ወቅት ከተሳታፊዎች የሚነሱ (ድንኳንና ተያያዥ አገልግሎቶችን በሚመለከት) ጥያቄዎችን ያስተናግዳል፤
8) ከበዓሉ መጠናቀቅ በኋላ ለኤግዚቢሽኑ ተሳታፊዎች ንብረቶቻቸውን እንዲያነሱ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤
9) የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ኤግዚቢሽን በድምቀት እንዲከበር አስፈላጊውን የቴክኒክ እገዛ ያደርጋል።
10) ሌሎች በውል የተሰጡትን ስራዎች ያከናውናል።

## 13. የተሳታፊ ከተሞች፣ መ/ቤቶች፣ ድርጅቶችና ባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

1) የኤግዚቢሽኑን ዓላማ ባገናዘበ መልኩ እና ይህ መመሪያ በሚያዘው መሰረት ይዘው የሚያቀርቧቸውን ዝግጅቶች ያደራጃሉ፤ ያጠናቅቃሉ፤
2) በኤግዚቢሽኑ ቦታ ቢያንስ ከሁለት ቀን በፊት ቀድመው በመገኘት ቦታቸውን ይረከባሉ፣ በተረከቡት ቦታ ላይ ብቻ ኤግዚቢሽናቸውን ይገነባሉ፤ አነስተኛ መሳሪያዎችን እንደ ፕላስተር፣ ሁክ ፕላስቲክ ገመድ፣ ሚስማር፡ ሜትር፣ የመጀመሪያ ደረጃ የሕክምና እርዳታ ወዘተ… በራሳቸው ይሸፍናሉ።
3) በበዓሉ ወቅት በኤግዚቢሽኑ ቦታ በመገኘት ለጎብኝዎች መግለጫ ይሰጣሉ፣ ጥያቄዎችን ያስተናግዳሉ፤
4) ከበዓሉ ማጠቃለያ በኋላ የገነቡትን ኤግዚቢሽን እና ንብረቶቻቸውን ከአንድ ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ያነሳሉ፤
5) ኤግዚቢሽናቸውን ለመገንባት እና ለማፍረስ አስፈላጊውን የሰው ኃይል ያቀርባሉ።
6) የኤግዚቢሽ ቦታና ድንኳን የከተሞች ፎረምን ዓላማ ለማሳካት ብቻ ይጠቀማሉ፤ ሆኖም የኤግዚቢሽኑን ቦታና ድንኳን የከተሞች ፎረም ካስቀመጠው ዓላማ ዉጪ መጠቀም ፈጽሞ የተከለከለ ነው።

## 14. የሁሉም ክልል የከተማ ልማትና ቤቶች ዘርፍ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

1) ሁሉም የክልሉ ከተሞች በበቂ ዝግጅት እንዲሳተፉ ያስተባብራሉ፣ ያነሳሳሉ፤ ለዝግጅቶቻቸውም ድጋፍ ያደርጋሉ፤
2) የኤግዚቢሽን መመሪያውን ዋና ዋና ጉዳዮች/ጭብጦች ተሳታፊ ከተሞች በግልጽ አውቀው እንዲሳተፉ ያደርጋሉ፤
3) በከተሞች ፎረም ዝግጅት ላይ ለመሳተፍ የአቅም ውስንነት ላለባቸው የክልሉ ከተሞች ድጋፍ ያፈላልጋሉ፤ ያስተባብራሉ፤
4) ከክልሉ መገናኛ ብዙሀን ጋር በመተባበር የከተሞች ፎረም ኩነቶችን እና የከተሞችን ኤግዚቢሽን በሚመለከት መረጃ ይሰጣሉ፣ ኩነቶችን በስፋት ያስተዋውቃሉ።

## 15. የኢትዮጵያ ከተሞች ትብብር መድረክ ተግባርና ኃላፊነት

ለ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የኤግዚቢሽንና የከተሞች ምዝገባ ሥራ እንዲሳካ መዝጋቢ ሙያተኛ ይመድባል፣

## ክፍል ሶስት

## የኤግዚቢሽኑ ይዘት እና ጥራት

## 16. የኤግዚቢሽኑ ይዘት

1) የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በዋነኝነት በከተሞች፣ በነዋሪዎች እና በባለድርሻ አካላት መካከል የመረጃ እና የልምድ ልውውጥ የሚካሄድበት ስለሆነ ይዘቱም ከንግድ ወይም ከሽቀጥ ልውውጥ ኤግዚቢሽን የተለየ ሆኖ በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ በናሙናዎች፣ በፎቶግራፎች፣ በፖስተሮች፣ በቻርቶች እና አጭር ፊልም የሚቀርብ ይሆናል፣
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከተሞችም ሆኑ ሌሎች ተሳታፊዎች በኤግዚቢሽኑ ላይ የእራሳቸውን ምርቶች ለገበያ ማቅረብ ይችላሉ፣
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከተሞች የሚያቀርቡት ኤግዚቢሽን በዋነኝነት ማንጸባርቅ ያለበት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና ቀጥሎ በአንቀጽ 17 የተገለጸውን ይሆናል፣

## 17. የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረምን ዓላማ ባገናዘበ መልኩ የተሳታፊ ከተሞች ኤግዚቢሽን የሚከተለው ይዘት እና ቅደም ተከተል ይኖረዋል፡-

| ተ.ቁ | ይዘት | የአቀራረብ ስልት |
|---|---|---|
| 1) | አጠቃላይ የከተማ መረጃ | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም ...ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>• ስም<br>• የህዝብ ብዛት<br>• ራዕይ<br>• ሎጎ<br>• የከተማው ልዩ መገለጫ...ወዘተ |

| | | |
|---|---|---|
| 2) | የከተማ የልማታዊ አመራር አቅም ግንባታ ስራዎች | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም …ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>• የለዉጥ ስራዊት ማፍራትና ማጎልበት ሥራዎች፡<br>• የአመራርና ፈጻሚ አፈጻጸም እውቅና ግብረመልስ ሥራዎች፡<br>• የአሰራርና አደረጃጀት ዝርጋታ ሥራዎች፡<br>• የጥናት ሥራዎች፡<br>• የእቅድ አፈጻጸም ክትትል፡ ግምገማ እና ምዘና እና ትግበራ ሥራዎች፡<br>• የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታ ቤዝ ሥራዎች፡<br>• የልማታዊ ኮሙኒኬሽን ሥራዎች |
| 3) | የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም …ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>• የተፈጠሩ የስራ እድሎች ጠቋሚ መረጃ /ግራፎች፣ ፖስተሮች ፎቶዎች …ወዘተ<br>• የሴቶችና ወጣቶች እንዲሁም አጠቃላይ የህ/ሰቡ ተጠቃሚነት የሚያንጸባርቁ ስራዎች |
| 4) | የከተሞች የልማታዊ መልካም አስተዳደር ስራዎች<br>• የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ስራዎች /ቁራ፣ እሳት አደጋ፣ ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ ወዘተ.. /<br>• የነዋሪዎች ተሳትፎና ንቅናቄ፣ በከተሞች አገልግሎት አሰጣጥና የሰው ሀይል ልማት ላይ ያለው ተሞክሮ | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም …ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>• በከተማ ልማት ዘርፎች እና በከተማ አቀፍ እንቅስቃሴዎች የነረዎችን ተሳትፎ ነረዎች የከተማውን ሰላም ለመጠበቅ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ የሚገልፁ ፎቶግራፎችና ሌሎች ሰነዶች፤<br>• ሴቶች፣ ወጣቶች፣ የአካል ጉዳተኞች… በከተማ ልማት ያላቸው ተሳትፎ የሚያሳይ ሰነድ፤<br>• በነዋሪዎች ብቻ፣ ከግልና ከመንግስት ተቋማት ጋር የተሰሩ ስራዎች<br>• የከተማው አደረጃጀትና የሚሰጠው አገልግሎት እስከ ቀበሌ ስለመውረዱና የሰው ኃይል ስለመሟላቱ፤<br>• በከተማው አገልግሎት አሰጣጥ የህብረተሰቡ አስተያየት፤ |
| 5) | የከተማ ፕላን፣ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ሪፎርም፣ | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም …ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>❖ የከተማ ፕላን<br>• መዋቅራዊ ፕላኖች፣<br>• የአካባቢዎች ፕላን ሞዴሎች፣<br>• የመሬት ዝግጅትና አቅርቦት ዋና ዋና ክንውኖች የሚገልፁ ግራፎች፣ ፎቶዎች ወዘተ…<br>• ካዳስተር የከተማ ካርታዎች ወዘተ…<br>❖ መሬት ልማትና ማኔጅመንት<br>• የከተማውን ግንባታና ክፍት ቦታ ለመለየት የተደረገ ጥረት፣<br>• የለማ መሬት ዝግጅት፣<br>• ለልማት የቀረበ መሬት፣<br>• ያስገኘው ገቢ፣ |
| 6) | የመኖሪያ ቤቶች ልማትና አስተዳደር | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም …ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>• በመኖሪያ ቤት የህብረት ሥራ ማኅበራት የተሰሩ ቤቶች፣<br>• የጋራ መኖሪያ ቤቶች ሞዴሎች ፎቶግራፎች ከነዋሪዎች ጋር፣<br>• በግል ሪል ስቴት፣ በግል ባለሃብቶችና በግለሰብ የተሰሩ ቤቶች፣<br>• የአቅርቦት እና ፍላጎት ማመሳከሪያ ግልፅ ቻርቶች፣ ፖስተሮች …ወዘተ<br>• የቤቶች ልማትን ተከትሎ የተፈጠሩ የስራ ዘርፎች መረጃ እና የስራ ዘርፎች ናሙና …ወዘተ |

| | | |
|---|---|---|
| | | • የወጣቶችና የሴቶች ተጠቃሚነት |
| 7) | የከተሞች የተቀናጀ መሰረተ ልማት አቅርቦት ስራዎች /ኮብልስቶን፣ የፍሳሽ ማስወገጃ ቦዮች፣ ወዘተ/ | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም ...ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>• የፕሮጀክቶች ሞዴል፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮችና ቻርቶች ...ወዘተ<br>• የመሰረተ ልማት መስፋፋትን ተከተሎ የተፈጠሩ የስራ መስኮችና ሌሎች ምቹ ሁኔታዎችን የሚያሳዩ ፎቶዎች ናሙናዎች ...ወዘተ<br>• የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ዓይነት እና የነዋሪው ተጠቃሚነት<br>• የከተማው የአተገባበር ስልት/ሂደት<br>• በአካባቢ መሰረተ ልማት አቅርቦት ላይ የሕ/ሰቡ ተሳትፎ |
| 8) | የከተሞች የአረንጓዴ ልማትና የዕዳት ማሻሻያ ሥራዎች | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም ...ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>• ከተማዋ የከተሞች ዕዳትና አረንጓዴ ልማት ስራዎችን ለማሳካት የተፈጠረ የሕዝብ ንቅናቄ፣<br>• የከተማዋን ጽዳትና ውበት የሚያሳይ ሰነድ፣ እንደዚሁም የመንገድ ላይ፣ የአደባባይ፣ መናፈሻ ቦታዎች፣ ተቋማት...ወዘተ የአረንጓዴ ልማት ሥራዎች፣ |
| 9) | የከተሞች ገቢ(ፋይናንስ) ልማትና አመራር | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም ...ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>• የካፒታል ፋይናንስ እጥረትን ለመፍታት የተደረገ ጥረት<br>• የገቢ ምንጮችና አቅም በመለየት የተሰሩ ሥራዎች፣<br>• የፋይናንስ አጠቃቀም<br>• የተሰበሰበ የማዘጋጃ ቤታዊ የገቢ መጠን ጠቋሚ መረጃዎች፣<br>• በተሻሻለ የፋይናንስ ስርዓት የተገኙ ውጤቶችን የሚያሳዩ መግለጫዎች /ፎቶግራፍ ፖስተር ፊልም ወዘተ/<br>• የፋይናንስ ማኑዋሎችን የግብር ከፋዮች መረጃ<br>• ለመሰረተ ልማት፣ ለኢንዱስትሪ ማስፋፊያ እና ለሌሎች የወጣ ወጪ ወዘተ. |
| 10) | ለህዝብ ተደራሽና ደህንነት የሚያረጋግጥ የከተማ ልማት ሥራዎች | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም ...ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>• የሴቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት<br>• የአካል ጉዳተኞች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት<br>• ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥ የስራ እድል መፍጠር ስልት በመከተል የተሰሩ ስራዎች<br>• በልማት ስራዊት አግባብ የተከናወኑ የተፋሰስ ልማት ስራ ስራዎች<br>• በከተሞች የእሳትና ድንገተኛ አደጋ መከላከያ ተቋማትን በማደራጀት የተሰሩ ስራዎች |
| 11) | ኢንቨስትመንት (ታላላቅ) | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም ...ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>• የከተማዋ የኢንቨስትመንት መስህቦች፣<br>• በከተማዋ ለኢንቨስትመንት የተዘጋጁ ምቹ ሁኔታዎች፣<br>• አሁን ያለው የኢንቨስትመንት መጠን እና ዓይነት መግለጫ፣<br>• የማመልከቻ ቅፆችና ጠቃሚ አድራሻዎች፣<br>• የኢንቨስትመንት ውጤቶች (ለማስተዋወቅ ወይም ለሽያጭ የሚቀርቡ)<br>• ባለሀብቶች በከተማው ያላቸውን ኢንቨስትመንት ማስተዋወቅ |
| 12) | ቱሪዝም/ባህል | በበራሪ ወረቀቶች፣ በሞዴሎች፣ ናሙናዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች አጭር ከ5 ደቂቃ ያልበለጠ ፊልም ...ወዘተ የሚቀርቡ፡-<br>• የቱሪስት መስህቦች ፎቶ፣ ማስታወቂያዎች፣ ፊልሞች፣ |

| | | |
|---|---|---|
| | | • የቱሪስት መረጃዎች /በራሪ ወረቀቶች ወይም ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጁ ጽሁፎች/፣ |
| 13) | ሌሎች | • የከተማዋን ሁኔታና ዕድገት የሚጠቁሙ መረጃዎች |

## 18. የኤግዚቢሽኑ ዝቅተኛ የጥራት መስፈርቶች

1) ተሳታፊ ከተሞች የኤግዚቢሽን አቀራረባቸው ከላይ የተቀመጠውን የይዘት ቅደም ተከተል የጠበቀ መሆን አለበት፣
2) በጽሑፍ የሚቀርቡ መረጃዎች በግልጽ የሚነበቡ እና ግድፈት የሌለባቸው መሆን አለባቸው፤ በተጨማሪም በእጅ ያልተጻፉ (በኮምፒዉተር የተጻፉ) እና ባለቀለም መሆን አለባቸዉ፣
3) የመረጃ ቻርቶች ባለቀለም፣ በግልጽ የሚታዩ፣ በእጅ ያልተዘጋጁ መሆን ይኖርባቸዋል፤ በሚታይ ሁኔታም መሰቀል አለባቸው፤ የቻርቶቹ መጠን ከA3 መጠን ያላነሰ መሆን አለበት፣
4) የመረጃ ዶክሜንተሪ ፊልሞች ርዝመት ከ5 ደቂቃ በላይ መሆን የለባቸውም፤
5) ፎቶ ግራፎች በጥራት የተነሱ ገላጭ እና ለጎብኚዎች ወይም ለእይታ አመቺ መጠን ያላቸው መሆን ይገባቸዋል፤
6) ለኤግዚቢሽን የሚቀርቡ የፎቶ ግራፎች መጠን ከA4 መጠን ያላነሰ መሆን አለበት፤
7) ተሳታፊ ከተሞች ከኤግዚቢሽናቸው ይዘት በተጨማሪ ጥራት ላለው አቀራረብ በርትተው መስራት ይጠበቅባቸዋል።
8) የኤግዚቢሽኑ ዝቅተኛ የጥራት መስፈርቶች በዋነኘነት የሚመለከተው ከተሞችን ሲሆን ሌሎች ተሳታፊዎች የሚያቀርቡት ዝግጅት ለፎረሙ የሚመጥን መሆን አለበት።

## 19. ለጎብኚዎች የሚደረግ ገለጻ

1) ተሳታፊ ከተሞች ከኤግዚቢሽኑ መክፈቻ እስከ መዝጊያው ድረስ ለእንግዶች ተገቢውን ገለጻ የሚያደርጉ ባለሞያዎችን መመደብ ይጠበቅባቸዋል፣
2) ገለጻ ሰጪዎች በኤግዚቢሽን ዝግጅት ላይ ገለጻ የማድረግ ልምድ ሊኖራቸው ይገባል፣
3) በመክፈቻው ቀን ለሚጎበኙ የክብር እንግዶች የሚሰጥ ገለጻ ለ5 ደቂቃ ያህል ይሆናል።

# ክፍል - አራት

# የኤግዚቢሽን ቦታ አሰጣጥ፣ አጠቃቀም እና የተሳትፎ ክፍያ

## 20. የኤግዚቢሽን ቦታ አሰጣጥ እና አጠቃቀም

1) አንድ ተሳታፊ የሚሰጠው አነስተኛ የቦታ መጠን 12 ካሬ ሜትር ሲሆን ከፍተኛው ከ600 ካሬ ሜትር መብለጥ የሌለበት ሆኖ በአንቀጽ 20 ንኡስ አንቀጾች 1፣ 2 እና 3 መሰረት በከተሞች ፍላጎት የሚወሰን ይሆናል፤
2) ምዝገባ የሚከናወነዉ መዝጋቢዉ አካል ወይም ኤግዚቢሽን ዝግጅትና የከተሞች ምዝገባ ንዑስ ኮሚቴ ከተሞች በባንክ የከፈሉበት ደረሰኝ ሲደርሰዉ ይሆናል።

3) የኤግዚቢሽን ቦታ ድልድል የሚካሄደው ተሳታፊ ከተሞች በሚያቀርቡት የቦታ ጥያቄ መሰረት ሆኖ በኤግዚቢሽን ንዑስ ኮሚቴ አማካኝነት የሚከናወን ይሆናል፡፡ ይህም በሚከተለው ሂደት ይከናወናል፡-

   ሀ/ ተሳታፊ ከተሞች የሚፈልጉትን የቦታ መጠን እስከ የካቲት 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ያሳውቃሉ፤

   ለ/ ተሳታፊዎች ለሚፈልጉት ቦታ የሚጠበቀውን ክፍያ እስከ መጋቢት 10 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ገቢ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፤

   ሐ/ ተሳታፊዎች የሚጠይቁት የቦታ መጠን ከሚፈቀደው ከፍተኛ የቦታ መጠን በላይ ከሆነ እንደ አስፈላጊነቱ በኤግዚቢሽን ንዑስ ኮሚቴ ውሳኔ ተሰጥቶበት አስፈላጊውን ክፍያ እንዲፈፅሙ ተደርጎ ሊሰጣቸው ይችላል፤

   መ/ ማንኛውም ተሳታፊ በኤግዚቢሽኑ ቦታ የተዘጋጀለትን ቦታ ለመረከብ ሲቀርብ የክፍያ ማረጋገጫ ደረሰኝ ወይም የባንክ የገንዘብ ትራንስፈር ማስረጃ ማቅረብ አለበት፤

   ሠ/ ለተሳታፊዎች የሚሰጠው ቦታ በእጣ የሚወሰን ሆኖ ትላልቅና ትናንሽ ከተሞችን በማቀላቀል ይደለደላል፤

   ረ/ የኤግዚቢሽን ቦታ አሰጣጥ (የኤግዚቢሽን ምዝገባና ቦታ የመደልደል ሥራ) በከተሞች ፎረም የኢግዚቢሽን ዝግጅትና የከተሞች ምዝገባ ንኡስ ኮሚቴ ይከናወናል፤

4) የኤግዚቢሽኑ ተሳታፊዎች ከኤግዚቢሽኑ መክፈቻ 2 ቀን በፊት ቦታቸውን ይረከባሉ፤

5) የኢግዚቢሽኑ ተሳታፊዎች ኤግዚቢሽኑ ከሚከፈትበት ቀን ዋዜማ የዲስፕሌይ ዝግጅቶቻቸውን ማጠናቀቅ አለባቸው፡፡ በኤግዚቢሽኑ መክፈቻ ወቅት ማንኛውንም የግንባታ እና የዲስፕሌይ ዝግጅት ማከናወን በጥብቅ የተከለከለ ነው፤

6) የኤግዚቢሽኑ ቦታ በየዕለቱ ከጠዋቱ 1:00 ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ 2:00 ሰዓት ድረስ ለተሳታፊዎች እና ጎብኚዎች ክፍት ይሆናል፤

7) የወሰዱትን ድንኳን ወይም ቦታ ለሦስተኛ ወገን ሙሉ በሙሉ አሳልፎ መስጠት የተከለከለ ነው፤ ያለአግባብ ሲጠቀም የተገኘ ሶስተኛ ወገን እንዲለቅ ይደረጋል፤ ቦታውን አሳልፎ ለሶስተኛ ወገን በሰጠ አካልም አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል፤

8) የተሳታፊዎችን ንብረት ደህንነት ለመጠበቅ እንዲያመች ከምሽቱ 2:00 ሰዓት እስከ ጠዋቱ 1:00 ሰዓት በኤግዚቢሽኑ ቦታ ከጥበቃ አባላት በስተቀር ማንም እንዲገኝ አይፈቀድም፡፡

## 21. የተሳትፎ ክፍያ

1) በኤግዚቢሽኑ ለመሳተፍ፡፡

   ሀ/ የምዝገባ ክፍያ

   - ለመጀመሪያዉ ዙር የULGDP 19 ተጠቃሚ ከተሞች ብር 2,500.00

- ለሁለተኛዉ ዙር የULGDP 26 ተጠቃሚ ከተሞች ብር 2,000.00
- ለሌሎች ከተሞች ብር 1,500.00

ለ/ ለሁሉም ከተሞች የቦታ ኪራይ ለአንድ ቀን በካሬ ሜትር ብር 250.00 መክፈል ይጠበቅባቸዋል፡፡

2) ተሳታፊዎች የኤግዚቢሽን ቦታውን የሚከራዩት ለ7 ቀን ብቻ ነው፤

3) ተሳታፊዎች የሚጠይቁት የቦታ መጠን ቀጥሎ በሰንጠረዥ ከተመለከተው ከ12 እስከ 600 ካሬ ሜትር ብቻ ይሆናል፤ ልዩ ሁኔታዎች ሲገጥሙ በልዩ ሁኔታ እንዲስተናገዱ ይደረጋል፡፡

| ተ.ቁ | የሚቀርቡ ቁሳቁሶችና አገልግሎቶች ዝርዝር | መግለጫ | መለኪያ |
|---|---|---|---|
| 1) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 600 ካሬ ሜትር (30X20) | በቁጥር |
| 2) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 500 ካሬ ሜትር (25X20) | በቁጥር |
| 3) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 400 ካሬ ሜትር (20X20) | በቁጥር |
| 4) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 300 ካሬ ሜትር (15X20) | በቁጥር |
| 5) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 200 ካሬ ሜትር (10X20) | በቁጥር |
| 6) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 150 ካሬ ሜትር (10X15) | በቁጥር |
| 7) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 100 ካሬ ሜትር (10X10) | በቁጥር |
| 8) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 80 ካሬ ሜትር (10X8) | በቁጥር |
| 9) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 60 ካሬ ሜትር (10X6) | በቁጥር |
| 10) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 40 ካሬ ሜትር (8X5) | በቁጥር |
| 11) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 20 ካሬ ሜትር (5X4) | በቁጥር |
| 12) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 16 ካሬ ሜትር (4X4) | በቁጥር |
| 13) | ድንኳን፣ ጠረጴዛና ወንበር | 12 ካሬ ሜትር (4X3) | በቁጥር |

4) ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አካላት የቦታ ክፍያ አይመለከታቸውም፡-

ሀ/ ከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት፣

ለ/ የኤች. አይ. ቪ. ግንዛቤ ማስጨበጫና የበጎ ፈቃደኝነት ምርመራ፣

ሐ/ ያለክፍያ ተመጣጣኝ የድንኳን መጠን የሚሰጣቸው ድርጅቶች፣ መስሪያ ቤቶችና ተቋማት /ቀይ መስቀል፣ እሳት አደጋ፣ የጤና ተቋማት፣ የጸጥታ አካላት፣ ወዘተ/ ካለው ቦታ አንጻር ታይቶ በ7ኛው የከተሞች ፎረም ቴክኒክ ኮሚቴ ሊወሰን ይችላል፡፡ ጎንደር ከተማ አዘጋጅ ከተማ በመሆኗ 600 ካሬ ሜትር በነጻ የሚሰጣት ሲሆን ከ600 ካሬ ሜትር በላይ ከጠየቀች ለተጨማሪው የቦታ መጠን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ) በተቀመጠው የኪራይ ዋጋ መሰረት የምትስተናገድ ሆና የቦታ ምርጫዋም ይጠበቅላታል፡፡

## 22. የድምጽ አጠቃቀም

1) ኤግዚቢሽኑን ብሎም ሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ዝግጅቶችን በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን ይቻል ዘንድ የበዓሉ ቦታ ለመደማመጥና መግለጫዎችን በተገቢው ሁኔታ ለመስጠት ምቹ መሆን አለበት፤

2) ተሳታፊዎች የሚጠቀሙባቸው እንደ ሙዚቃ፣ የቴሌቪዥን ማስታወቂያዎች፣ ፊልሞች፣ መግለጫዎች፣ ወዘተ የመሳሰሉት ድምፅ የሚያወጡ ግብዓቶች ከተሞች በሚወጣላቸው ፕሮግራም መሰረት መሆን አለበት፤ ካልተቻለም በአካባቢያቸው ያሉትን ሌሎች ተሳታፊዎች በማያውክ ሁኔታ መጠቀም ይጠበቅባቸዋል፤

3) ከተሳታፊ ከተሞች የሚለቀቀው የሙዚቃ ድምጽ መጠን ከ 60 DB መብለጥ የለበትም፡፡

4) የድንጽ ማጉያ ወይም የሙዚቃ መሳሪያ በመጠቀምም ሆነ በሌላ መንገድ ሙዚቃ ማሰማት የሚቻለው ከቀኑ 6፡00 ሰዓት እስከ 8፡00 ሰዓት ድረስ ባለው ጊዜ ብቻ ነው፤ ከዚህ ጊዜ ውጭ ሙዚቃ ማሰማት አጥብቆ የተከለከለ ነው፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከተገለጸው መጠን በላይ የሆነ እና አካባቢን የሚያውኩ ድምጾችን የሚያመነጭ ተሳታፊ ከተማ ወይም ከተፈቀደው ሰዓት ውጭ ሙዚቃ የሚያሰማ ተሳታፊ ከተማ ሆኖ ከተገኘ፡-

   ሀ) ለመጀመሪያ ጥፋት/መተላለፍ የቃል ማስጠንቀቂያ ያስጠዋል፣

   ለ ለሁለተኛው ጥፋት/መተላለፍ አጠቃላይ ከተማው ከሚያገኘው ነጥብ 10 በመቶ እንዲቀነስ ይደረጋል፣

   ሐ) ለሶስተኛው ጥፋት/መተላለፍ የድምጽ ማጉያ መሳሪያዎሪያውን እስከ ኤግዚቢሽኑ ፍጻሜ ድረስ እንዲያስረክብ ይደረጋል፡፡

## 23. የጊዜ ሰሌዳ

የኤግዚቢሽን ዝግጅቱ ዋና ዋና ተግባራት በሚከተለው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ይከናወናሉ፡-

| ተ.ቁ | ተግባር | ቀን |
|---|---|---|
| 1) | የአውደ ርዕይ ተሳትፎ ምዝገባና የቦታ መጠን ጥያቄ ማቅረብ | እስከ የካቲት 30/2009 |
| 2) | የቦታ እና የምዝገባ ክፍያ ማጠናቀቅ | እስከ መጋቢት 10/2009 |
| 3) | የኤግዚቢሽን ቦታ ዝግጅት፣ የመብራት እና ውሃ አቅርቦት፣ የአጥር ግንባታ፣ የመጸዳጃ ቤቶች ግንባታ፣ የቆሻሻ መጣያ ቦታዎች ዝግጅት ወዘተ. ማጠናቀቅያ | እስከ መጋቢት 30/2009 |
| 4) | የድንኳን ተከላና ማስዋብ እና የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ማጠናቀቅ | እስከ ሚያዚያ 19/2009 (ከኤግዚቢሽን መክፈቻ ከ2 ቀናት በፊት) |
| 5) | የኤግዚቢሽን ግንባታ ማጠናቀቂያ | እስከ ሚያዚያ 19/2009 |
| 6) | የኤግዚቢሽን ቦታ ርክክብ | እስከ ሚያዚያ 20/2009 ጠዋት 2፡ 30 ሰዓት |
| 7) | የኤግዚቢሽን መክፈቻ | ሚያዚያ 22/2009 |
| 8) | የአውደ ርዕይ ማጠናቀቂያ | ሚያዚያ 28/2009 |
| 9) | የአውደ ርዕይ ቁሳቁስ ማንሻ | ሚያዚያ 29/2009 |

## ክፍል - አምስት

## የኤግዚቢሽን ዝግጅት ወጪዎች እና የበጀት ምንጭ

### 24. የኤግዚቢሽን ዝግጅት ወጪዎች

የኤግዚቢሽን ዝግጅት ወጪዎች የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡-

1) የቦታ ዝግጅት ወጪዎች (የቦታ ድልደላን፣ የአጥር ግንባታን፣ የመብራት እና የውሃ መስመር ዝርጋታን ለማከናወኑ የወጡ ወጪዎች)
2) የድንኳን ኪራይ፣
3) የአርክቴክቸራል እና ኤሌክትሪካል ፕላን፣
4) የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ፣ የድንኳን ተከላ እና ማፍረሻ
5) አስፈላጊ የኤግዚቢሽን ቁሳቁሶች (ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ የኤሌክትሪክ ገመድ፣ መደሻ ወዘተ… የመሳሰሉት) ኪራይና ግዥ ወጪዎች ናቸው፡፡

### 25. የኤግዚቢሽን ዝግጅት የበጀት ምንጭ

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ኤግዚቢሽን ወጪዎች የበጀት ምንጭ ከጎንደር ከተማ፣ ከተሳታፊ ከተሞች የተሳትፎ ክፍያ እና ለኤግዚቢሽን ዝግጅቱ ከአዘጋጆችና ከስፖንሰሮች የሚሰበሰበው ገንዘብ ነው፡፡

## ክፍል - ስድስት

## ስለኤግዚቢሽኑ መረጃ ስለማግኘት

### 26. ኤግዚቢሽንን በሚመለከት መረጃ ስለማግኘት

1) የ7ኛውን የከተሞች ፎረም የኤግዚቢሽን ምዝገባ በተመለከተ የአስተባባሪዎች ስልክ ቁጥር 0115531688 ወይም 0115540633 ወይም 0115150556 እንደዚሁም በሞባይል ቁጥር 0934480214 በመደወል መረጃ ማግኘት ይችላሉ፤
2) ተሳታፊዎች የኤግዚቢሽን ቦታ ጥያቄ፣ የምዝገባና ክፍያን የሚመለከቱ መረጃዎች በስልክ ቁጥር 0115541253 ወይም 0115541291 ወይም በሞባይል ቁጥር 0912854457 ወይም 0911505261 በመደወል ማግኘት ይቻላል፤
3) ተሳታፊዎች ለመመዝገቢያ እና ለቦታ የሚከፍሉትን ክፍያ "**በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር- የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም**" "Ministry of Urban Development & Housing — Ethiopian Urban Forum" የባንክ ሂሳብ ቁጥር **1000191468655 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ** ገቢ በማድረግ በከተማው ስም ገቢ የተደረገበት ማስረጃ በፋክስ ቁጥር 0115541268 ወይም 0115510332 ወይም 0115540630 ወይም 0115541292 ለ7ኛው የከተሞች ፎረም ተብሎ ኮፒው መላክ ይኖርበታል፡፡

### 27. ኃላፊነቱን በማይወጣ አካል ላይ ስለሚወሰድ እርምጃና ቅጣት

1) ተባባሪ አዘጋጁ የኤግዚቢሽን ድንኳን ተከላ እና የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ሥራን የከተሞች ፎረም በዓል ከሚጀመርበት ሁለት ቀናት (ሚያዚያ 20/2009 ዓ.ም በጠዋቱ 2:30) ቀድሞ

ኮሚሽነሩ ሲጠቀምባቸው ድንኳኖች ከሚከፈለው ጥቅል ክፍያ ላይ 10 በመቶ ተቀንሶ ለመ/ቤቱ ገቢ ይደረጋል።

2) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ ተባባሪ አዘጋጁ ግንባታ ለመፈጸም በተቀመጠው መርሐ-ግብር መሰረት ኤግዚቢሽን በሚካሄድበት ቦታ ላይ ሚያዚያ 20/2009 ዓ.ም ጠዋቱ 2:30 ተገኝቶ ግንባታውን በሙሉ ካላከናወነ መ/ቤቱ አስፈላጊውን እማራጭ የሚወስድ ሆኖ ለሚፈጠረው ኪሳራ ተባባሪ አዘጋጁ ኃላፊነት አለበት፡፡

## 28. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ይህንን መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ሊያሻሽለው ይችላል።

## 29. የተሻሩ መመሪያዎች

የ6ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የኤግዚቢሽን ዝግጅት መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## 30. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ --------- ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አምባቸው መኮንን (ዶ/ር)

የኢፌዲሪ ከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ሚኒስትር